

**በፕሬዘደንት**
**ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ**
*የቀዳሚ አመራር*
*ሁለተኛ አማካሪ*

# በክብ መዞር

የሚሄድበት የጠፋባቸው ሰዎች በክብ ይዞራሉ የሚለውን የጥንት አባባልሰምታችኋልን?

የጀርመን የስነ አእምሮ ዶክተር የነበረው ጃን ኤል. ሱማን ይህ እውነት እንደሆነ ለማወቅ በጥናት ለመወሰን ፈለገ። በዚህ ጥናቱ ተሳታፊ የሆኑትን ወደ ትልቅ ደናማ አካባቢ እና ወደ ሰሀራ በረሀ ወሰዳቸው እናም በአለም የት እንደሚገኙ በሚታይበት መሳሪያ የት እንደሄዱ ተመለከተ። አቅጣጫ መለያ መሳሪያ ወይም ሌላ ምንም መሳሪያዎች አልነበሯቸውም። የተሰጣቸውም መመሪያ ቀላል ነበር፥ በተመለከተላቸው አቅጣጫ በቀጥታ ሂዱ።

ዶክተር ሱማን ምን እንደተከሰተ እንዲህ በማለት ገለጸ። “[አንዳንዶቹ] ዳመና በተሸፈነበት ቀን፣ ጸሀይ በዳመና በተሸፈነችበት [የት እንደሚገኙ ለመጥቀስ የሚችሉበት ምንም ሳይኖራቸው] ተጓዙ። . . .[እነርሱም] በክብ ዞሩ፣ [አብዛኛዎቹም] እነርሱ የተጓዙበትን መንገን ሳይገነዘቡ ደጋግመው አለፉበት። ሌሎች ተሳታፊዎችም ጸሀይ እየበራ፣ የሚጠቅሱባቸው ነገሮች በሩቅ እየታዩአቸው፣ ይሄዱ ነበር “እነዚህም. . .በፍጹም ቀጥተኛ የሆነ መንገድ ይከተሉ ነበር።”[1]

ይህ ጥናት ሌሎች የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ተደጋግመው ነበር።[2] ሁሉም አንድ አይነት የሆነ ውጤት አግኝተው ነበር።

ሰዎች ለመመልከት የሚችሉት የምድር ምልክት ሳይኖራቸው ሲቀር በክብ ይዞራሉ።

## የቅዱሳት መጻህፍት ምልክቶች

ያለ መንፈሳዊ ምልክቶች፣ ሰውም ይቅበዘበዛል። ያለ እግዚአብሔር ቃል፣ እኛም በክብ እንዞራለን።

እንደ ግለሰብ እና እንደ ህብረተሰብ፣ ከጊዜ መጀመሪያ ጀምሮ በእያንዳንዱ ዘመናት ይህ አካሄድ ሲደጋገም እንመለከታለን። የእግዚአብሔርን ቃላት ስናጣ፣ እንጠፋለን።

ለዚህም ነው ሌሂ ልጆቹን የነሀስ ሰሌዳውን እንዲያመጡ ወደ እየሩሳሌም እንዲልካቸው ጌታ ያዘዘው። የሌሂ ትውልዶች በትክክል መንገድ ላይ እንዳሉ ለመወሰን የሚችሉበት መመሪያ የሚሰጧቸው የሚመኩበት ምልክቶች እንደሚያስፈልጋቸው እግዚአብሔር አውቆ ነበር።

ቅዱሳት መጻህፍት የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። እነዚህም ወደ አዳኛችን እንድንቀርብ እና ብቁ የሆኑትን አላማዎች እንድንደርስባቸው ለመጓዝ የሚያስፈልጉንን መንገዶች የሚያሳዩ የእግዚአብሔር ምልክቶች ናቸው።

## የአጠቃላይ ጉባኤ ምልክቶች

በአጠቃላይ ጉባኤ የሚሰጡ መመሪያዎች በትክክለኛ መንገድ ላይ እንዳለን ለማወቅ የሚረዱን ሌላ ምልክቶች ናቸው።

አንዳንዴ እራሴን “በቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ የተናገሩትን ወንዶችና ሴቶች ቃላቶች አዳምጫለሁኝን? ቃላቶቻቸውን ደጋግሜ አንብቤአለሁኝን? አሰላስሌአቸዋለሁኝን እናም በህይወቴ ተጠቅሜባቸዋለሁኝን? ወይም ጥሩውን ንግግር ተደስቼበት እናም በመንፈስ የተመሩ መልእክቶች በህይወቴ ለመጠቀም ችላ ብያለሁኝን? በማለት እጠይቃለሁ።”

ምናልባት ስታዳምጡ ወይም ስታነቡ፣ አንድ ወይም ሁለት ነጥቦችን ጽፋችኋል። ምናልባት አንድ ነገርን በተሻለ መንገድ ወይም በተለየ ሁኔታ ለማድረግ ወስናችኋል። ስላለፈው አጠቃላይ ጉባኤ መልእክቶች አስቡበት። ብዙዎቹ ቤተሰቦቻችንን እንድናጠናክር እና ጋብቻችንን እንድናሻሽል አበረታትተውናል። ይህ የ *Liahona* መፅሔትም ህይወታችንን ከሚባርኩ ሀሳቦች ጋር በእነዚህ ዘለአለማዊ መሰረታዊ መርሆ ላይ ያተኩራል።

እነዚህ ጠቃሚ ምክሮችን እስተውለናል ወይ? እናም

እንጠቀምባቸዋለን? እነዚህን እውነተኛ እና ዋጋ ያላቸውን ምልክቶች እያወቅን ወደ እነርሱ እየተጓዝን ነው ያለነውን?

**የመንከራተቴ መድሀኒት**

መንፈሳዊ ምልክቶች በቀጥተኛው እና በጠባብ መንገዱ ላይ እኛን ለመጠበቅ በጣም አስፈላጊ ናቸው። መጓዝ ስለሚገባን መንገድ ግልጽ መመሪያው ይሰጣሉ፣ ነገር ግን ይህን የሚሰጡት ካወቅናቸው እና ወደ እነርሱ ከሄድን ብቻ ነው።።

በእነዚህ ምልክቶች ለመሄድ እምቢ ካልን፣ ትርጉም የሌላቸው፣ ጌጥ ከመሆን በላይ ምንም ጥቅም የሌላቸው እና ወደ ፊት የሚታየውን ለውጥ እንዲኖረው የሚያሳዩ ብቻ ይሆናሉ።

በእስተያየታችን ብቻ መሄድ የሚበቃ አይደለም።

መልካም ፍላጎት መኖሩ ብቻ የሚበቃ አይደለም።

በተፈጥሮ ባለን አስተያየት ላይ ብቻ መመካትም በቂ አይደለም።

ቀጥተኛ የሆነ መንፈሳዊ መንገድ እንደምንከተል በምናስብበትም ጊዜ፣ መመሪያ የሚሰጡን ምልክቶች ሳይኖረን፣ ያለመንፈስ መመ ሪያ፣ እንንከራተታለን።

ስለዚህ፣ አይኖቻችንን እንክፈት እናም በጎ አድራጊ አምላካችን ለልጆቹ የሰጠውን ምልክቶች እንመልከት። እናንብብ፣ እናም የእግ ዚአብሔርን ቃላት እንጠቀምባቸው። በእውነተኛ ፍላጎት እንጸልይ እናም የመንፈስን ምሪት እናዳምጥ እና እንከተል። በሚያፈቅረን የሰማይ አባታችን የተሰጡትን ከሰማይ የመጡትን ምልክቶች ስናውቅ፣ መንገዳችንን በእነርሱ እናስተካክላለን። ወደ መንፈሳዊ ምልክቶችም አቅጣጫችንን በየጊዜው በማስተካከል መንገዳችንን ማቅናት ይገባናል።

በዚህም መንገድ፣ በክብ አንንከራተትም እናም በልበ ሙሉነት እና በእርግጠኛነት በክርስቶስ ደቀ መዛሙርትነት በጠበበና በቀጠነ መንገድ ለሚጓዙት ውርስ ወደሆነው ወደዚያ ታላቅ ሰማያዊ በረከት እንሂድ።

**ማስታወሻዎች**

1.1. Jan L. Souman and others, "Walking in Circles," *Current Biology* (Sept. 29, 2009), 1538, cell.com/current-biology/issue?pii=S0960-9822(09) X0019-9 ተመልከቱ።
2.2. ለምሳሌ፣ "A Mystery:: Why Can't We Walk Straight?" ተመልከቱ። npr.org/blogs/krulwich/2011/06/01/131050832/ a-mystery-why-can-t-we-walk-straight።

---

**ከዚህ መልእክት ማስተማር።**

ከዚህ መልእክት ለማስተማር ስትዘጋጁ፣ በመንፈሳዊ ምልክቶች ስለተመሩ ሰዎች ወይም በክብ ስለተንከራተቱ ሰዎች በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ምሳሌዎችን ለመፈለግ ትችላላችሁ። ጥናታችሁን በእነዚህ ቅዱሳት መጻህፍት ለመጀመር ትችላላችሁ፥ ዘኍልቁ 14፥26–33፤ 1 ኔፊ 16፥28–29፤ አልማ 37፥38–47። ምሪትን ከተቀበላችሁም፣ ከእነዚህ ምሳሌዎች አስተያየታችሁን ከምታስተምሯቸው ጋር ለመካፈል ትችላላችሁ። ከእነዚህ ታሪኮች ምን ለመማር እንደሚችሉ ጠይቋቸው።

## ወጣቶች

### ለእናንተ ምልክቶች

ፕሬዘደንት ኡክዶርፍ አጠቃላይ ጉባኤን እና ቅዱሳት መጻህፍትን በመንፈዝ እንዳንንከራተት እንደሚረዱን ምልክቶች ገልጸዋቸዋል። ህይወታችሁን ያነሳሷችሁን እና የመሯችሁን ሌሎች መንፈሳዊ ምልክቶችን አሰላስሉባቸው። አጋጣሚዎቻችሁን በማስታወሻዎቻችሁ ጻፉ። እነዚህ ከፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ. ሞንሰን የተጠቀሱትም ሊረዷችሁ ይችላሉ፥

"የፔትሪያርክ በረከታችሁ ከሁሉም በላይ ጭለማ የሆኑትን ምሽቶች ረድቶ ያሳልፍላችኋል። በህይወት አደጋዎች ውስጥም ይመራችኋል። በረ ከታችሁ በጥንቃቄ የሚታጠፍ እና የሚሸጎጡ አይደሉም። በፍሬም ውስጥ የሚቀመጥ ወይም የሚታተምም አይደለም። ነገር ግን፣ መነበብ ይገባዋል። መወደድ ይገባዋል። መከተል ይገባዋል።"

"Your Patriarchal Blessing: A Liahona of Light," *Ensign*, ህዳር 1986, 66

"የሰማይ አባታችን በደህና እንድንመለስ ለማረጋገጥ ከእርሱ መመ ሪያ የምንቀበልበት መንገድ ሳይሰጠን በዘለአለም ጉዞአችን አልላከንም። የምናገረውም ስለ ጸሎት ነው። የምናገረውም በጸጥተኛው እና ትንሽ ድምጽ ስለሚያሾኮሽከው ነው።

"The Race of Life," *Liahona*, May 2012, 92።

## ልጆች

### መንገዴን ለማግኘት እችላለሁ

ፕሬዘደንት ኡክዶርፍ ትክክለኛውን ለመምረጥ እና ወደ አዳኝ ለመ ቅረብ ስለሚያስችሉን መንፈሳዊ ምልክቶችን መከተል ያስፈልገናል ብለዋል። አንዳንዶቹ ምልክቶችም ጸሎት፣ ቅዱሳት መጻህፍት፣ አጠቃላይ ጉባኤ፣ እና *Liahona.* ናቸው።

ከቤተሰባችሁ ጋር ካለፈው አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ ንግግርን አንብቡ። በትክክለኛው መንገድ ለመቆየት ተነጋጋሪው ምን እንድናደርግ ሀሳብ ያቀር ባሉ? የተማራችሁትን ለመጠቀም ከቤተሰባችሁ ጋር አላማ አድርጉ።

© 2013 በ Intellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/12 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/12 (እ.አ.አ) *First Presidency Message, June 2013* (እ.አ.አ) Amharic። 10666 506

# በቤተሰብ ታሪክ መደሰት

*ይህን መልእክት አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው። ለተጨማሪ መረጃ ወደwww.reliefsociety.lds.org ሂዱ።*

**እምነት • ቤተሰብ • እርዳታ**

የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል ሽማግሌ ራስል ኤም. ኔልሰን የኤልያስ መንፈስ “መንፈስ ቅዱስ ስለቤተሰብ መለኮታዊ ፍጥረት ምስክር ሲሰጥ የሚታይበት ነው” በማለት አስተምረዋል።[1]

በዳግም እንደተመለሰቸው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንደመሆናችን መጠን፣ ያለፉ ትውልዶቻችንን የመፈለግ እና የሚያድን የወንጌል ስነ ስርዓቶችን የመስጠት ቃል ኪዳን የገባንበት ሀላፊነት አለብን። እነርሱ ካለእኛ “ፍጹም ለመሆን አይችሉም” (ዕብራውያን 11፥40)፣ እናም “እኛም ያለ ሙታኖቻችን ፍጹም ለመሆን አንችልም” (ት. እና ቃ. 128፥15)።

የቤተሰብ ታሪክ ስራ ለዘለአለም ህይወት በረከቶች ያዘጋጀናል እናም እምነታችንን እና የግል ጻድቅነታችንን እንድናሳድግ ይረዳናል። የቤተሰብ ታሪክ የቤተክርስቲያኗ ተልዕኮ ዋና ክፍል ነው እናም ለሁላችንም የደህንነት እና የዘለአለማዊነት ስራ እንዲቻል ያደርጋል።

የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዘደንት፣ ፕሬዘደንት ቦይድ ኬ ፓከር፣ እንዳሉት፥ “የራሳችንን ትውልዶች ስንፈልግ ከስም በላይ ለማወቅ እንፈልጋለን። . . . ይህም ፍላጎት ልባችንን ወደ አባቶቻችን ያዞራል—እነርሱን ለማግኘት እና ለማወቅ እናም ለማገልገል እንፈልጋለን።[2]

## ከቅዱሳት መጻህፍት

ሚልክያስ 4፥5–6፤ 1 ቆሮንቶስ 15፥29፤ ት. እና ቃ. 124፥28–36፤ 128፥15

## ከታሪካችን

ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንዳስተማረው፣ “እግዚአብሔር ከሰጠን በዚህ አለም ካለው ሀላፊነቶች ታላቁ ሙታኖቻችንን መፈለግ ነው።[3] በቤተመቅደስ ለሞቱት ትውልዶቻችን በውክልና ለማገልገል እና ለእነርሱ አስፈላጊ የሆኑትን ስነ ስርዓቶችን ለማከናወን እንችላለን።

የ14 አመት ልጇ የሞተባት በናቩ፣ ኢለኖይ የኖረች ሳሊ ራንዶል በዘለአለም ቤተሰቦች ቃል ኪዳን ታላቅ መፅናኛን አግኝታ ነበር። ባለቤቷ በውክልና ለልጇ ከተጠመቀ በኋላ፣ ለዘመዶቿ እንዲህ ጻፈች፥ “እኛ ለሞቱት [ትውልዶቻችን] መጠመቅ እና ለማወቅ እስከምንችልበት ድረስ እነርሱን ለማዳን ለማዳን መቻላችን. . .እንዴት ግሩም ነገር ነው።” ከዚያም ዘመዶቿ ስለትውልዶቻቸው መረጃዎች እንዲልኩላት እንዲህ በማለት ጠየቀቻቸው፣ “[ቤተሰባችንን] ለማዳን የምችለውን ለማድረግ አላማ አለኝ።”[4]

ማስታወሻዎች

1. ራስል ኤም. ኔልሰን, “A New Harvest Time,” *Liahona,* July 1998, 34።
2. ቦይድ ኬ. ፓከር፣ “Your Family History: Getting Started,” *Liahona,* Nov. 2011, 17።
3. Teachings of Presidents of the Church: Joseph Smith [2007 (እ.አ.አ)]፣ 475
4. Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society (2011)፣ 20–21 ተመልከቱ።

### ምን ማድረግ እችላለሁ?

1. የምጠብቃቸው እህቶች የቤተሰብ ታሪክን እንዲፈልጉ ለመርዳት ምን ማድረግ እችላለሁ?
2. የግል ታሪኬን እየቀረጽኩኝ ነውን?

© 2013 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/12 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/12 (እ.አ.አ) *Visiting Teaching Message, June 2013* (እ.አ.አ) Aharic። 10666 506